ኪዳነ ምሕረት

የካቲት ፲፮ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም.

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ "ቃል ኪዳን" የሚለው ቃል 257 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል፤ ኪዳን ማለት ቃል "ተካየደ" ከሚለው ከግእዝ ቃል የወጣ ሲኾን "ተዋዋለ፣ ተስማማ፣ ተማማለ" ማለትን ሲያሳይ እግዚአብሔር ሰውን ከማፍቀሩ የተነሣ ለሰው ልጅ እንደ ባልንጀራ አድርጎ መሐላን ይምላል፣ ቃል ኪዳንም ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስን ስናብብ በብሉይም ኾነ በሐዲስ እግዚአብሔር አምላክ ለወዳጆቹ ለምርጦቹ ቅዱሳን ቃል ኪዳንን ገብቷል። ክቡር ዳዊት በመዝ 88፡2-3 ላይ "እንዲህ ብለሃልና። ምሕረት ለዘላለም ይመሠረታል፥ እውነትህም በሰማይ ይጸናል ከመረጥኋቸው ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ" እንዳለ ከኹሉም ቅዱሳን በላይ ኾና ሰማይ ምድር የማይወስኑትን አምላክ በማሕፀኗ ለመሸከም፣ ኪሩቤል ሱራፌል ዙፋኑን በመፍራትና በመንቀጥቀጥ የሚሸከሙትን ሰማያዊ መለኮትን በዝርባዋ ለማዘል፣ በክንዷ ለመታቀፍ፣ ሰማይ ምድር ከፊቱ የሚሸሹትን የባሕርይ አምላክን በከናፍሮቿ ለመሳም፣ ፍጥረታትን ኹሉ በዝናብ አብቅሎ በፀሓይ አብስሎ የሚመግበውን፤ ለቅዱሳን መላእክት ርሱ የገለጸላቸው ምስጋና ምግብ ኩኗቸው እንዲኖሩ ያደረገውን ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተካከለውን እግዚአብሔር ወልድን የድንግልና ጡቶቿን ለማጥባት ከተመረጠች ከእናቱ ጋር የገባው ጽኑዕ የምሕረት ቃል ኪዳን እጅግ ልዩ እና ለታጥኣን ኹሉ ተስፋ የሚኾን ነው።

መልአከ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤልም በአምላክ እናት ፊት ቆሞ "ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አግኝተሻልና አትፍሪ" በማለት ከፍጡራን ወገን ማንም ሊያገኘው የማይችለውን ይኸውም በልዑል እግዚአብሔር ዘንድ መወደድን በማግኘት ከባለሟልነት ኹሉ የላቀ ባለሟልነት ይኸውም የአምላክ እናት የመኾንን የማማለድ ልዩ ጸጋና ክብር እንደተሰጣት ነግሯታል። መልአኩ በዚኽ ምስጋናው ላይ "ሞገስን አግኝተሻልና" አለ እንጂ "ወደ ፊት ታገኛለሽ" አለማለቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ጥንቱኑ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የተጠበቀችና በልዑል የተመረጠች መኾኗን የሚያረጋግጥም ነበር። ከዚኽ ከተሰጣት ታላቅ ባለሟልነት የተነሣ ልጇን በማሳሳብ ውሃው ወደ ወይን እንዲለወጥ አስደርጋለች (ዮሐ 2፡1-10)። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ እንደምናነብበው በአምላካቸው ፊት ባለሟልነትን ያገኙ ብዙዎች ቅዱሳን ቢኖሩም ቅሉ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ግን ለነዚኽ ኹሉ ቅዱሳን ሰማያዊ ክብርን ቃል ኪዳንን የሰጠውን አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና በሞውለዷ "ወላዲተ አምላክ" የመባል ታላቅና ልዩ ባለሟልነት ተሰጥቷታልና የርሷ ክብር ከማንም ቅዱሳን ክብር ጋር ፈጽሞ የማይነጻጸር ነው።

ከ 432-447 ዓ.ም ሴሌኡሲያ ላይ ጳጳስ የነበረው ሊቁ ባስልዮስም እግዚአብሔር ለእናቱ የሰጣት ልዩ ባለሟልነትን ከቅዱሳን ጋር በማነጻጸር ሲጽፍ "What encomiums can we offer her as she deserves, when everything of this world is beneath her merits?..." (የሚመጥናትን ምን ዐይነት ልዩ ምስጋና እናቅርብላት? የዚኽ ዓለም ነገር ኹሉ አይመጥናትምና፤ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ቅዱሳን ሲናገር "ዓለም አልተገባቸውም" (ዕብ ፲፩፥፴፰) ካላቸው፤ ለአምላክ እናትማ ከከዋክብት በላይ ኾና እንደምታበራው ፀሓይ ለኾነችው ለርሷ ምን ልንል እንችል ይኾን? (ራእ ፲፪፥፩)... ምን ምስጢር እንደተከናወነ ተመልከት፤ ኅሊናንና አእምሮን የሚያልፍ ነገር እንደኾነ አስተውል፤ ታዲያ የአምላክን እናት ታላቅነት ኹሉም ሰው እንደምን አይናገር? ማንስ ነው ከቅዱሳን ኹሉ በላይ እንደኾነች ያላስተዋለ? እግዚአብሔር ላገልጋዮቹ የሚልቅ ጸጋን ከሰጠና የሚነኩት ኹሉ ሰው ከበሽታው ከተፈወሰ፤ ጥላቸው ያረፈበት ተአምር ከተፈጸመለት፤ ጴጥሮስ በጥላው ካደነ (የሐዋ ፭፥፲፭)፤ የጳውሎስ የልብሱ ጨርቅ ዕራፊ መናፍስትን ካወጣ (የሐዋ ፲፱፥፲፩)፤ ለእናቱማ ምን ዐይነት ሥልጣንና ኀይል ተሰጥቷት ይኾን?... ለቅዱሳኑ ይኽነን ያኽል ድንቅ እንዲያደርጉ ባለሟልነትን ከሰጣቸው ወልዳ ላሰደገችው እናቱማ ምን ያኽል ይሰጣት ይኾን? በምን ዐይነትስ ስጦታ አስጊጧት ይኾን? ጴጥሮስ "ክርስቶስ አንተ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ

ነኽ” ስላለው ብፁዕ ከተባለና የመንግሥተ ሰማያት ቍልፍ ከተሰጠው (ማቴ ፲፮፥፲፮-፲፱)፤ ርሷ ከኹሉም ይልቅ እንዴት የተባረከች (ብፅዕት) አትኾን? (ሉቃ ፩፥፵፰)፤ ጳውሎስ ታላቅ ክብር ያለውን የክርስቶስን ስም በመሸከሙ “ምርጥ ዕቃ” ከተባለ (የሐዋ ፱፥፲፭)፤ የአምላክ እናትማ የምእመናን ምግብ የኾነ መናውን ሳይኾን የሕይወት ሰማያዊ እንጀራን ያስገኘች ርሷ ምን ዐይነት ልዩ ዕቃው ትኾን?... ነገር ግን ስለርሷ ብዙ እናገራለኍ ብዬ ስለክብሯ ጥቂት በመናገር ራሴን በኀፍረት ውስጥ እንዳልጨምር እፈራለኍ ስለዚኽ ካኹን ወዲኽ የንግግሬን መልሕቅ ስቤ በዝምታ ወደቤ ላይ ማረፍን መርጬአለኍ) በማለት በእግዚአብሔር ፊት የተሰጣት ባለሟልነት ፍጹም እንደኾነና ከቃላት በላይ እንደኾነ አስተምሯል።

ዳግመኛም ቅዱሳን መላእክትና ጻድቃን ካገኙት ሞገስ የተነሣ ወደ ፈጣሪያቸው እንዲያማልዱን ስንማጸናቸው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ግን የአምላክ እናት ናትና ካገኘችው ከዚኽ ታላቅ ባለሟልነት የተነሣ ወደተወደደው ልጇ እንድታማልደን እንማጸናታለን፤ ከዚኽም የተነሣ ነው ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም በእሑድ ውዳሴ ማርያም ላይ “ለኪ ይደሉ ዘእምኩሎሙ ቅዱሳን ትሰአሊ ለነ ኦ ምልእተ ጸጋ...” (ጸጋን የተመላሽ ሆይ ከቅዱሳን ኹሉ ይልቅ ትለምኚልን ዘንድ ላንቺ ይገባል፤ አንቺ ከሊቃነ ጳጳሳት ትበልጪያለሽ፤ ከነቢያትም ከመምህራንም ትከብሪያለሽ ከሱራፌልና ከኪሩቤል ግርማ የሚበልጥ የመወደድ ግርማ አለሽ፤ በእውነቱ የባሕርያችን መመኪያ አንቺ ነሽ) በማለት ያመሰገናት።

ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም ካገኘችው ታላቅ ባለሟልነት የተነሣ ፭ሺሕከ፭፱ ዘመን ሲፈጸም ያለ ዘርዐ ብእሲ አካላዊ ቃል ክርስቶስን በኀቱም ድንግልና የፀነሰች፤ ፱ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ የተሸከመች፣ በኀቱም ድንግልና የወለደች፣ በክንዷ የታቀፈች፣ በዣርባዋ ያዘለች ርሷ ብቻ ናትና፤ በርሷ አማላጅነት የምናቀርበው ጸሎት ምን ያኽል ታላቅ እንደኾነ በሰዓታት መጽሐፉ ላይ፡- “ወፈድፋደሰ በእንተ ማርያም እምከ እንተ ይእቲ ትምክህተ ዘመድነ ...” (ይልቁንም የባሕርያችን መመኪያ ስለምትኾን ስለ እናትኽ ስለ ማርያም አንተን በመፅነስና አንተን በመውለድ ዕድፍ ጉድፍ ስላላገኘው ስለ አልተለወጠ ድንግልናዋና ስለ ተሸከመኽ ማሕፀኗ፤ ስለ ታቀፉኽ ስለ ክንዶቿና፣ ስለ ዳሰሱኽ ስለ እጆቿ፤ ስለ ሳሙኽ ስለ ከንፈሮቿ ስለ አሳደጉኽ ስለ ጡቶቿ፤ ከአንተ ጋር ስለ ተመላለሱ ስለ እግሮቿና፤ ስለ ዐዘለኽ ስለ ዣርባዋ፤ ብሩሃት ስለሚኾኑ ስለ ዐይኖቿ በጎ መዐዛ ስላላቸው አፍንጮቿ፤ ጸዐዶች ስለሚኾኑ ጥርሶቿ፤ በመልአኩ በገብርኤል ቃል ስለ ተበሠሩ (ብሥራትን ስለ ሰሙ) ስለ ዣሮቿ፤ ከርሷ ስለነሣኽው ሥሮችና ጸጕር፣ ደምና፣ ዐፅም ስለ ነፍስና ሥጋ፤ አባቶቻችን እንደ አስተማሩን ፈጽሞ ያለመለየትና ያለመለወጥ ከመለኮትነትኽ ጋራ አንድ ያደረግኸው) በማለት እንዳስተማረ፤ በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ባለሟልነት እንዳገኘች በብርሃናዊዉ መልአክ የተመሰከረላት የአምላካችን እናት ቅድስት ድንግል ማርያምን ከልጇ ታማልደን ዘንድ “ሰአሊ ለነ ቅድስት” (ቅድስት ሆይ ለምኝልን) እያልን እንማጸናታለን።

ይኸውም ታላቁ የነገረ ማርያም መጽሐፍ እንደሚያስረዳን ጌታችን ካረገ በኋላ እመቤታችን ጌታችን ወደ ተቀበረበት ጎልጎታ እየኼደች ትጸልይ ነበር፤ ከዕለታት ባንዳቸው በየካቲት ፲፮ ዕለት ስትጸልይ “አዕረግዋ ውስተ ሰማይ ከመ ያርእይዋ መካነ ዕረፍቶሙ ለጻድቃን ኀበ ሀለዉ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ ወተቀበልዋ ኩሎሙ ነፍሳተ አበው እለ አዕረፉ እምአዳም እስከኔሁ ወሰገዱ ላቲ እንዘ ይብሉ ስብሐት ለእግዚአብሔር ዘፈጠረ ለነ ኪያኪ ሥጋ እምሥጋነ ወዐፅመ እምዐፅምነ” ይላል መላእክት አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብ ያሉበትን የጻድቃን የማረፊያቸውን ቦታ ያሳዩዋት ዘንድ ወደ ገነት አሳረጓት፤ በዚያም ከአዳም ዝምሮ እስከዚያው ያረፉ ያባቶች ነፍሳት ተቀብለዋት “ከዐፅማችን አንቺን ዐጥንት ከሥጋችን አንቺን ሥጋ ለፈጠረልን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባው” እያሉ የአክብሮት ስግደት ሰግደውለታል።

ከዚያም መላእክት የጻድቅ ሰው ነፍስ ከሥጋው ሲለይ ያለውን ፍጹም ክብርና የሚወርሰውን የገነት ርስቱን መላእክት ካሳዩዋት በኋላ፤ ኃጥኣን ነፍሳቸው ከሥጋቸው ሲለይ ያላቸውን ጭንቅ ነፍሳቸው በሲኦል የምትቀበለውን ከፍተኛ መከራ አሳዩዋት፤ “ወሶበ ተስእኖሙ አምስጦ ይቤሉ እንዘ ይኬልሑ ኦ እግዝእትነ

እሙ ለመድኅን ወለተ ብርሃን ንዒ ኀቤነ ከመ ትፍትሕነ እማእሰሪሁ ለሰይጣን ወኢትኅድግነ” ይላል ለማምለጥ ባልተቻላቸውም ጊዜ “የመድኅን እናቱ የብርሃን መገኛ እመቤታችን ሆይ ከዚኽ ከዲያብሎስ ቍራኝነት ታላቅቂን ዘንድ ድረሺልን ቸል አትበዪ” እያሉ ምልጃዋን ሸተው በታላቅ ጩኸት ያለቅሱ ዝመር።

ያን ጊዜ ርኅርኅት የኾነች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም “ወይ ሎሙ ወአሌ ሎሙ መኑ እምዜነዎሙ ለውሉደ ሰብእ ኢይምጽኡ ዝየ” (ወዮላቸው ወዮታ አለባቸው ወደዚኽ እንዳይመጡ ለሰው ልጆች ኹሉ ማን በነገራቸው) እያለች ስታለቅስ፤ መላእክትም ለርሷ “ኢትፍርሂ ኦ ማርያም እስመ እግዚአብሔር ምስሌኪ ወምስለ እለ የአምኑ ብኪ” (እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ስለኾነና ባንቺ አማላጅነት ከአመኑት ኹሉ ጋር ስለ አለ አይዞሽ) በማለት ነገሯት።

ርሷም “እስእለከ እግዚኦ ወአስተበቍዐከ በእንተ ኩሉ ዘየአምን ብየ ረስዮ እግዚኦ ግዑዘ እምሲኦል ተዘኪረከ ረኃበ ወጽምዐ ወኩሎ መከራ ዘረከበኒ ኀቤከ ወምስሌከ” (አቤቱ በኔ ቃል ኪዳን ስላመነ ኹሉ እማልድኻለኁ እለምንኻለኁ፤ መራቤን መጠማቴንም ካንተ ጋር በምድረ ግብጽ ያገኘኝን ረኃብና ጥም ኹሉ አስበኽ አቤቱ ወደ ሲኦል ከመውረድ ነጻ አድርገው) በማለት ወደ ልጇ ፍጹም ልመናን ባቀረበች ጊዜ ጌታችን ተገልጾላት “ይኩን በከመ ትቤሊ እፈጽም ለኪ ኩሎ መፍቅደኪ አኮኑ ተሰባእኩ በእንተ ዝንቱ መሐልኩ ለኪ በርእስየ ከመ ኢይሔሱ ኪዳንየ” (የለመሺዉን ኹሉ ይደረግልሽ፤ የምትፈቅጂውን ኹሉ እፈጽምልሻለኁ የለመንሺዉን ኹሉ ላደርግልሽ ሰው ኹኜአለኹና፤ መሐላዬን እንዳላፈርስ አማንየ በርእስየ ብዬ በራሴ ማልኹልሽ) ሲል ለእናቱ የማያልፍ የምሕረት ቃል ኪዳንን ገብቶ ገብቶላታልና በዓሉ “ኪዳነ ምሕረት” በመባል ይታሰባል።

ሊቁ ቅዱስ ያሬድም በዝማሬው ላይ ጌታ ለእናቱ ስለገባላት ቃል ኪዳን፡- “ይቤላ ለእ ማርያም እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ተካየድኩ ምስሌኪ ኪዳነ ምሕረት ከመ አድኅን ዘተአመነኪ መሐልኩ ለኪ በርዕስየ ዘመሐልኩ አነ ለኖኅ ገብርየ ወለአብርሃም ፍቁርየ፤ ዘመሐልኩ አነ ለዳዊት ኅሩይየ ብእሲ ምእመን ዘከመ ልብየ መሐልኩ ለኪ በርዕስየ በቅዱስ ሥጋየ ወበክቡር ደምየ መሐልኩ ለኪ በርዕስየ ከመ ኢይሔሱ ማእኰትየ” (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ማርያምን እንዲኽ አላት በምልጃሽ ያመነብሽን አድን ዘንድ ካንቺ ጋራ የምሕረት ቃል ኪዳንን ተጋባኁ፤ ለአገልጋዬ ለኖኅና ለወዳጇ ለአብርሃም ቃል የገባኁ እኔ በራሴ ማልኹልሽ፤ እንደ ልቤ ለምለው ለታመነው ለዳዊት የማልኁ እኔ በራሴ ማልኹልሽ፤ በቅዱስ ሥጋዬና በክቡር ደሜ የማልኁ እኔ ምዬ እንደማልከዳ ማልኹልሽ) በማለት ጽፎታል።

በዚኽች በየካቲት 16 ዕለት በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የስምዖን (የበላኤ ሰብእ) ታሪክ ይነገራል። ቅምር በምትባል ሀገር ስምዖን የሚባል አንድ እጅግ ደግ ሰው ነበር፤ ይኽ ሰውም ጌታችን በማቴ ፳፭፥፴፭ ላይ “እንግዳ ብኾን ተቀብላችኹኛል” የሚለውን ትምህርቱንና ዳግመኛም ቅዱስ ጳውሎስ “የወንድማማች መዋደድ ይኑር፤ እንግዶችን መቀበል አትርሱ፤ በዚኽ አንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን እንግድነት ተቀብለዋልና” (ዕብ ፲፫፥፩-፪) ብሎ ያስተማረውን በማሰብ እንግዳን ተቀብሎ ማስተናገድን ይወድ ነበር፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በቀዳማዊ መልእክቱ ምዕ ፭፥፰ ላይ “ባለጋራችኁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራል” በማለት እንደተናገረው የበጎ ጠላት የኾነው ሰይጣንም በዚኽ ደግ ሰው ላይ በመቅናት ከፍተኛ ኀጢአት ውስጥ ሊጥለው ወዶ ጭፍሮቹን ወደ ስምዖን ቤት በሦስት መንገደኞች አምሳል ወደ ቤቱ ላከበት።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ፪ቆሮ ፲፩፥፲፬ ላይ “ይኽም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣል” በማለት እንዳስተማረ የዋሁ ስምዖን አጋንንት መኾናቸውን ባለማወቅ ወደ ቤቱ እንዲገቡ ለመናቸው፤ እነርሱም “ፈቃዳችንን ኹሉ እንድትፈጽምልን ማልልንና እንገባለን” አሉት፤ ርሱም በየዋህነት ጽኑ መሐላን በመማል ወደ ቤቱ አስገብቶ “ሰአሉ ዘትፈቅዱ ኦ አጋእዝትየ እፈጽም

ለክሙ” (ጌቶቼ የምትፈልጉትን ነገር ጠይቁ እፈጽምላችኋለው) አላቸው፤ አጋንንትም ስምዖንን “ልጅኽን ሠውተኽ ለእራት አዘጋጅልን” አሉት፤ ስምዖንም ይኽን እንደማያደርገው ቢነግራቸው እነርሱ “አስቀድመኽ ስመ እግዚአብሔር ጠርተኽ የገባኸው ቃል ይታበላልን” በማለት የከፋ ነገራቸውን ይናገሩ ዝመር። ርሱም መሐላውን በማሰብ አብርሃም ልጁን ለመሠዋት ልቡናውን እንዴት እንዳጨከነ ዳግመኛም ዮፍታሔ በተሳለው ስለት መሠረት የሚወዳት ልጁን ለመሥዋዕት እንዳቀረበ ዐስቦ ቤተ ሰቦቹ ሳያዩ ልጁን ዐርዶ ሥጋውን አቀረበላቸው (ዘፍ ፳፪፥፩-፲፫፤ መሳ ፲፩፥፴፬-፴)፤ አዳምንና ሔዋንን እግዚአብሔር ያላዘዛቸውን ዕፀ በለስን እንዲበሉ ያደረገ ጥንተ ጠላታችን ሰይጣን መጥፎ ድርጊት ካሠራ በኋላ በእጅጉ ወደ ከፋ ኀጢአት መውሰድ ልማዱ ነውና የልጁን ሥጋ እንዲቀምሰው በመገፋፋት ካስቀመሱት በኋላ አጋንንት ከርሱ ተሰወሩ።

ከዚያ በኋላ ይኽ ስምዖን ከእኽል ከውሃ ይልቅ ፍላጎቱ የሰው ሥጋን ወደ መብላት በመለወጥ ቤተ ሰቦቹን ጨምሮ በድምሩ ሰባ ስምንት ሰዎችን በልቷል፤ በዚኽ ምክንያት “በላኤ ሰብእ” (ሰውን የሚበላ) የሚል ሥያሜ ተሰጥቶታል፤ ከዚያም ሀብቱን ኹሉ ጥሎ ከቤቱ ወጥቶ አንዲት የውሃ ዕርኮት ይዞ ሲኼድ ኹለንተናው በደዌ ሥጋ የታመመ ድኻ ሰው አገኘ፤ ያም ሰው በጣም ተጠምቶ ነበርና በላኤ ሰብእ የውሃ ዕርኮት ይዞ ስላየው “አምላክን ስለ ወለደች ድንግል ማርያም ብለኽ ነፍሴ ከማለፏ በፊት ከያዝኸው ውሃ አጠጣኝ” በማለት ለመነው።

ያን ጊዜ በላኤ ሰብእ ወደ ልቡ በመመለስ አምላክ በማቴ ፲፥፵፩-፵፪ ላይ “ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፤ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል፤ ማንም ከእነዚኽ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውሃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለው ዋጋው አይጠፋበትም” በማለት ያስተማረው ትዝ ብሎት “በአማን አነሂ ሰማዕኩ እምንእስየ ከመ ይእቲ ሠናይት ወታድኅን በጸሎታ ወትባልሕ እምሲኦል ነዋ ይእዜ ተማሕፀንኩ ባቲ፤ ንሣእ ስተይ በእንተ ስማ ለቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ” (ይኽቺስ በእውነት መልካምና በአማላጅነቷም ከሲኦል የምታድን እንደኾነች ከሕፃንነቴ ዝምሬ ሰምቻለኹና በርሷ እማጸናለኹና አምላክን ስለ ወለደች ስለ ክብርት ድንግል ማርያም እንካ ጠጣ) በማለት ያለውን ውሃ ሰጠው።

ይኽም የስምዖንን ሃይማኖትንና ምግባርን የሚያሳይ ነው፤ ምክንያቱም አምላክን ስለወለደች ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ተብሎ ሲለመን መስጠቱ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት የባሕርይ አምላክ መኾኑን፤ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምም ወላዲተ አምላክ እንደኾነች የሚያምን እንደኾነ ቍርጥ እምነቱን ያሳየ ሲኾን፤ በተጨማሪም በውሃ ጥም ለተቃጠለው ነዳይ ያለውን ውሃውን መስጠቱ “ብጠማ አጠጥታችኹኛልና” የሚለውን የወንጌል ቃል መፈጸሙን ያለውን ምግባር ያሳየ ነው (ማቴ ፳፭፥፴፭-፴)።

በሉቃስ ወንጌል ምዕ ፲፩፥፲፱ ላይ ያ ከአባቱ ተለይቶ ያባቱን ንብረት አጥፍቶ የሚመገበውን ባጣ ጊዜ “ወደ አባቴ ልመለስ ልጅኽ ልባል አይገባኝም ከአገልጋዮችኽ እንደ አንዱ አድርገኝ እለዋለኹ” በማለት ወደ አባቱ ቤት እንደ ተመለሰው ታናሽ ልጅ ይኽ ስምዖንም በእጅጉ ስለ ኀጢአቱ በመጸጸት “እዜከር ሕማማ ለእግዝእትየ ማርያም ከመ በጽሐ ላዕሌሃ ረኃብ ወጽምዕ ወኩሉ ዘዘዚኣሁ በመዋዕለ ስደታ ዘምስለ ፍቁር ወልዳ” (አኹንም እመቤቴ ማርያም በስደቷ ወራት ከተወደደው ልጇ ጋር የደረሰባትን ረኃብና ጥም አስባለኹ) በማለት በጸምና በጸሎት እኽል ውሃ ሳይቀምስ ስለ ኀጢአቱ እያለቀሰ ከቆየ በኋላ በኻያ አንደኛው ቀን ሞተ፤ ወዲያው መላእክተ ጽልመት ነፍሱን ወደ ሲኦል ይወስዷት ዘንድ በማስፈራትና በማስደንገጥ ከበቧት፤ ያን ጊዜ እመቤታችን “መሐር ሊተ ኦ ወልድየ መሐር ሊተ ኦ እግዚእየ እስመ አስተየ ለነዳይ ማየ በእንተ ስምየ፤ ወአንተኒ ትቤለኒ ዘገብረ ተዝካረኪ ወዘጸውዐ ስመኪ ሕይወተ ዘለዓለም የሐዩ”

(ልጄ ጌታዬ ሆይ ማርልኝ በኔ ስም ለነዳይ ውሃ አጠጥቷልና፤ ስምሽን የጠራ መታሰቢያሽን ያደረገ የዘላለም ሕይወትን ያገኛል ብለኽ ቃል ኪዳን ገብተኽልኛልና) አለችው።

በኀጢአቱ ተጸጽቶ "አቤቱ በመንግሥትኽ በመጣኽ ጊዜ አስበኝ" ብቻ ላለው በቀኙ ተሰቅሎ ለነበረው ወንበዴ በሉቃ ፳፫፥፵፫ ላይ "ዛሬ በገነት ከኔ ጋር ትኖራለኽ" በማለት ምሕረትን የሰጠ ቸር ሰው ወዳጅ የኾነው ልጄም "መሐላዬን አላፈርስም፤ ሚዛን አምጥታችኁ ስለ እናቴ ያጠጣውን ያን ውሃ በአንድ ወገን፤ እኒያን ፸፰ ነፍሳት በአንድ ወገን አድርጋችኁ መዝኑት" በማለት መላእክትን አዘዛቸው፤ ያን ጊዜ "ማንም ከእነዚኽ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውሃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለው ዋጋው አይጠፋበትም" ያለው ቃሉ ሊፈጸም በእናቱ ስም ስምዖን ያጠጣት ውሃ መዘነች፤ ከዚኽ በኋላ በመድኀኔ ዓለም ቸርነት፤ በእናቱ በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት የስምዖን ነፍስ ምሕረትን አግኝታ ገነትን ለመውረስ በቅታለችና፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ይኽነን በመያዝ በዚኽ መጽሐፍ ላይ፡-

"ድካመ ጌጋይየ ትማእ ማርያም ጽድቀ ዚኣኪ በጽንዓ
መዳልወ ጥበብ ሶበ መልኣ ሰማኒተ ነፍሳተ ወሰብዓ
ሕፍነ ማይ ኀየለ ወሞአ"

"ማርያም የአንቺ ጽድቅ የበደሌን ድካም ድል ትነሣ ዘንድ የጥበብ (የምስጢር) ሚዛኖች በሙሉ ጊዜ እፍኝ ውሃ ሰባ ስምንት ነፍሳትን ፈጽሞ ድል ነሣ" በማለት ምስጢሩን እንደ ወርቅ አንከብሎ እንደ ሸማ ጠቅልሎ አስቀምጦታል።

ይኽ ስምዖን በእመቤታችን ቃል ኪዳን ስለ መዳኑ አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው ላይ

"ሚ ሠናይ ከመ ጼና ጽጌ ልሑይ
በኵሉ ጊዜ ምሒረ ነዳይ
በእንተ ኪዳንኪ ድንግል ለበላዔ ሰብእ ጊጉይ
ሶበ ዐብየ እምኀጢአቱ ክበደ መድሎቱ ለማይ
ለተአምርኪ በሰማይ ተገብረ ግናይ"

(ኹል ጊዜ ለደኻ መራራት መመጽወት እንደ ለመለመ አበባ ያማረ ነው (ምን ያምር?) ድንግል በቃል ኪዳንሽ ምክንያት ከበላዔ ሰብእ ኀጢአት የውሃ ሚዛን በልጦ በመታየቱ ለተአምርሽ በሰማይ ምስጋና ኾነ) በማለት ስምዖን በመድኀኔ ዓለም ቸርነት በእመቤታችን አማላጅነት ስለዳነ በወንጌል "እንዲኹ ንስሓ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሓ በሚገባ በአንድ ኀጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይኾናል" በማለት አምላካችን እንዳስተማረ በአንድ ሰው መዳን ደስ የሚላቸው መላእክት በሰማይ ምስጋናን ማቅረባቸውን ገልጸዋል (ሉቃ ፲፭፥፯)።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ የልጅሽን የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት፣ ፈራጂነት፤ ያንቺን ወላዲተ አምላክነት አማላጅነት የምናምን ልጆችሽን ከልጅሽ ከወዳጅሽ ታማልጂን ዘንድ እንማጸንሻለን።

ምንጭ ፡- መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ
ነገረ ማርያም - Mariology
https://www.facebook.com/Ngeremariam/posts/566140406893617:0?__tn__=K-R